የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# <u>ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህ.ወ.ሓ.ት) ከፖለቲካ ፓርቲነት መሠረዙን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ</u>

ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህ.ወ.ሓ.ት) በዐመጻ ድርጊት በመሣተፉ ምክንያት ቦርዱ በዐዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 98 መሠረት ከፖለቲካ ፓርቲነት መሠረዙ የሚታወስ ነው። ይሁንና የፕሪቶሪያ ስምምነት ከተደረገ በኋላ የህ.ወ.ሓ.ት ሕጋዊ ሰውነት እንዲሰረዝ የተላለፈው ውሣኔ እንዲነሣ ቦርዱን ሚያዝያ 13 እና ሚያዝያ 28 ቀን 2015 ዓ.ም. መጠየቁ የሚታወቅ ነው። ሆኖም ቦርዱ በዐመጻ ድርጊት በመሣተፍ ከፖለቲካ ፓርቲነት የተሠረዘ የፖለቲካ ፓርቲ ሕጋዊ ሰውነቱ ከተሠረዘ በኋላ ሕጋዊ ሰውነቱን ለመመለስ የሚያስችል ሕግ ስለሌለ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ግንቦት 4 ቀን 2015 ዓ.ም. በቁጥር አ1162/11/1155 በተጻፈ ደብዳቤ መልስ ሰጥቷል።

የኢትዮጵያ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር ዐዋጅ ቁጥር 1162/2011ን ለማሻሻል የወጣውን ዐዋጅ ቁጥር 1332/2016 መታወጁን ተከትሎ ህ.ወ.ሓ.ት በዐዋጁ መሠረት "በልዩ ሁኔታ" ፓርቲ ሆኖ ለመመዝገብ መቅረብ የሚገባቸውን ሠነዶች በማያያዝ ባቀረበው ጥያቄ እንዲሁም ህ.ወ.ሓ.ትን አስመልክቶ የፍትሕ ሚኒስቴር በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሰኔ 17 ቀን 2016 ዓ.ም. በቁጥር ፍሚ1/1345 በጻፈው ደብዳቤ መነሻ ህ.ወ.ሓ.ት ሕጋዊ ሰውነት የሚያገኝበትን ሕግ መሠረት በማድረግ ቦርዱ በማሻሻያ ዐዋጁ መሠረት ለፓርቲው "በልዩ ሁኔታ" መዝግቦ ነሐሴ 3 ቀን 2016 ዓ.ም. ሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሰጥቷል።

በዚህ መሠረት ህ.ወ.ሓ.ት በዐዋጅ ቁጥር 1332/2016፤ ይህንን ተከትሎ በወጣው መመሪያ ቁጥር 25/2016 እና ቦርዱ ምዝገባውን ተከትሎ እንዲፈጽም የሰጠውን ትዕዛዝ ባለማክበሩ ቦርዱ በተለያየ ጊዜ ማሳሰቢያ ቢሰጥም ፓርቲው ግን በሕግ የተጣለበትን ግዴታ አልፈጸመም። ከዚህም በላይ በዐዋጅ ቁጥር 1332/2016 መሠረት የፓርቲውን ሕጋዊነት የሚያረጋግጠውን ሰርተፊኬቱን በወቅቱ አምኖበትና ተስማምቶ ከቦርዱ

የተቀበለውን የፖለቲካ ፓርቲ ሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ አላውቅም፤ ሕጋዊ ሰውነቴ በዚህ ሠነድ አይረጋገጥም በማለት ሕግንና መመሪያን ባለማክበርና ለማክበርም ፈቃደኛ ባለመሆን ሲገልጽ ቆይቷል።

ቦርዱ በዐዋጅ ቁጥር 1162/2011 መሠረት በዐመጻ ተግባር በመሠማራቱ የተሠረዘን ፓርቲ ሕጋዊ ሰውነት የምመልስበት የሕግ ድንጋጌ የለኝም በማለት ግንቦት 4 ቀን 2015 ዓ.ም. ለህ.ወ.ሓ.ት ምላሽ ከሰጠ ከአንድ ዓመት በኋላ ዐዋጅ ቁጥር 1332/2016 ግንቦት 27 ቀን 2016 ዓ.ም. ሲታወጅ ህ.ወ.ሓ.ት ይህንኑ ፓርቲዎችን በልዩ ሁኔታ የሚመዘግብ ዐዋጅ በታወጀ በሁለተኛው ወር ሐምሌ 19 ቀን 2016 ዓ.ም. በዐዋጁ ላይ "በልዩ ሁኔታ" የፖለቲካ ፓርቲ ሆኖ ለመመዝገብ እንዲቀርቡ በሕጉ የተመለከቱትን ዝርዝር ሠነዶች ይኸውም የፓርቲውን ፕሮግራም፣ የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ እና የፓርቲው አመራሮች ስም ዝርዝር ከፊርማ ጋር ለቦርድ አቅርቧል።

በሌላ በኩል ህ.ወ.ሓ.ት ሕጋዊ ሰውነቱ እንዲሠረዝ የተላለፈውን ውሣኔ እንዲነሣ በማለት ሚያዝያ 13 እና ሚያዝያ 28 ቀን 2015 ዓ.ም. ለቦርዱ ባቀረበው ጥያቄ በዐዋጅ ቁጥር 1332/2016 “በልዩ ሁኔታ” ፓርቲ ሆኖ ለመመዝገብ እንዲቀርቡ የተጠየቁትን ሠነዶች አንዳቸውንም አያይዞ አላቀረበም። ይህ የሚያስረዳው ህ.ወ.ሓ.ት ሐምሌ 19 ቀን 2016 ዓ.ም. ያቀረበው ጥያቄ ሚያዝያ 13 እና ሚያዝያ 28 ቀን 2015 ዓ.ም. ካቀረበው ጥያቄ በተለየ መልኩ በዐዋጅ ቁጥር 1332/2016 መሠረት "በልዩ ሁኔታ" ፓርቲ ሆኖ ለመመዝገብ እንዲቀርብ ሕጉ በሚጠይቀው መሠረት የፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባ ጥያቄ ማቅረቡን ነው።

ህ.ወ.ሓ.ት ሐምሌ 19 ቀን 2016 ዓ.ም. ጥያቄውን ሲያቀርብ ዐዋጅ ቁጥር 1332/2016 ታውጆ፤ ለሕዝብ በይፋ ተገልጾ፤ በሥራ ላይ ከዋለ ሁለት ወር ካለፈው በኋላ ሲሆን፤ በዚህ ወቅት የዐዋጁ ዐላማ፣ አፈጻጸምና በዐዋጁ መሠረት "በልዩ ሁኔታ" ፓርቲ ሆኖ የመመዝገብ ሂደት በግልጽ የታወቀ በመሆኑ ህ.ወ.ሓ.ትም ይህንኑ ለሕዝብ ይፋ የሆነውን ዐዋጅ ዐላማና አፈጻጸም በግልጽ በማወቅና በመረዳት በዐዋጁ ላይ የተመለከቱትን ሠነዶች አያይዞ በማቅረብ በዐዋጁ የተጠየቀውን የምዝገባ ሥርዓት በመፈጸም ምዝገባው ተከናውኗል።

ከሁሉም በላይ ህ.ወ.ሓ.ት ሐምሌ 19 ቀን 2016 ዓ.ም. በጻፈው ደብዳቤ ላይ የቀድሞው ሕጋዊ ሰውነት ይመለስልኝ ቢልም፤ ያቀረባቸው ሠነዶች፤ ጥያቄው የቀረበው የዐዋጁን መውጣት ተከትሎ መሆኑና ፍትሕ ሚኒስቴር ስለህ.ወ.ሓ.ት ለቦርዱ የጻፈው ደበዳቤ "በልዩ ሁኔታ" ለመመዝገብ የቀረበ መሆኑን የሚያስረዳ ሲሆን፤ በተለይም ቦርዱ ለህ.ወ.ሓ.ት ነሐሴ 3 ቀን 2016 ዓ.ም. "በልዩ ሁኔታ" በመመዝገብ የሰጠው የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሠርትፊኬት፣ ከሠርትፊኬቱ ጋር አብሮ በሰጠው ነሐሴ 3 ቀን 2016 ዓ.ም. በቁጥር

አ1162/11/5180 በተጻፈ ደብዳቤ ላይ የህ.ወ.ሓ.ት የቀድሞው ሕጋዊ ሰውነት እንደማይመለስለት በግልጽ ተመልክቶ እያለ፤ የፓርቲው ከፍተኛ አመራር በቦርዱ ዋና መሥሪያ ቤት በመገኘት ሠርትፊኬቱንና ደብዳቤውን በሚገባ አይተው፣ አንብበውና ተስማምተው በፈቃዳቸው ፈርመው ከወሰዱ በኋላ ይህ "በልዩ ሁኔታ" ተመዝግቦ የተሰጠን የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ አንቀበለውም ማለት ተቀባይነት የለውም።

ቦርዱ በሕግ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣትና ፓርቲው ያለበትን ኃላፊነትና ግዴታ እንዲወጣ ለማድረግ በተለያየ ወቅት በጽሑፍ ማሳሰቢያ ሲሰጥ ቢቆይም፤ ፓርቲው ግዴታውን ባለመወጣቱ ቦርዱ "የኢትዮጵያ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር ዐዋጅ ቁጥር 1162/2011ማሻሻያ ዐዋጅ ቁጥር 1332/2016 እና ዐዋጁን" ተከትሎ በወጣው መመሪያ ቁጥር 25/2016 መሠረት ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ ሳይጠብቅ ፓርቲውን መሠረዝ የሚያስችል የሕግ መሠረት ቢኖረውም፤ ፓርቲው ግዴታውን እንዲወጣ ዕድል ለመስጠት ቦርዱ ፓርቲውን ለሦስት ወራት ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እንቅስቃሴ በማገድ ፓርቲው የዕርምት ዕርምጃ በመውሰድ በሕጉ መሠረት ግዴታውን እንዲፈጽም ቦርዱ ጥረት ቢያደርግም ፓርቲው የተጣለበትን የሕግ ግዴታ ለመወጣት ፈቃደኛ አልሆነም።

በመሆኑም ቦርዱ የካቲት 5 ቀን 2017 ዓ.ም. በቁጥር አ1162/11/15421 በተጻፈ ደብዳቤ ተራ ቁጥር 3 ላይ በተጠቀሰው የቦርዱ ውሣኔ ላይ ፓርቲው በሦስት ወር ዕግድ ጊዜ የዕርምት ዕርምጃ ሳይወስድ ቢቀር በዐዋጅ ቁጥር 1332/16 አንቀጽ 3(11) (ሐ) እና በመመሪያ ቁጥር 25 /2016 አንቀጽ 19(1)(ሐ) መሠረት ቦርዱ የተለየ አካሄድ ሳይከተል የፓርቲውን ምዝገባ እንዲሠረዝ ቦርዱ በወሠነው መሠረት ፓርቲው የዕርምት ዕርምጃ ባለመውሰዱ ቦርዱ ግንቦት 5 ቀን 2017 ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ፓርቲው ከግንቦት 5 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ ከፖለቲካ ፓርቲነት የተሠረዘ መሆኑን ወሥኗል። ይህም ውሣኔ ለህ.ወ.ሓ.ት፣ ለፍትሕ ሚኒስቴር በጽሑፍ እንዲደርስ፣ ለሕዝብ ይፋ እንዲደረግና የፓርቲውን መሠረዝ ውጤትን በተመለከተ የዐዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 99 እንደ አግባብነቱ በህ.ወ.ሓ.ትና አመራሮቹ ላይ እንዲፈጸም ቦርዱ ወሥኗል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

ግንቦት 6 ቀን 2017 ዓ.ም.

አዲስ አበባ